# ስለ ጋስትሮስኮፒ ምርመራ ገለጻ

*በሂሌል ያፌ የሕክምና ማዕከል*
*የጋስትሮኢንተሮሎግ ክፍል*

המרכז הרפואי
הלל יפה
מומחים באנשים

# የጋስትሮስኮፒ ምርመራ ምንድን ነው?



- ይህ ለላይኛው የመፍጫ ሥርዐት ክፍል በተጣጣፊ ቱቦ (ኢንዶስኮፒ) አማካይነት የሚደረግ ምርመራ ነው።
- የኢንዶስኮፒ መሣሪያ በሽታዎችን ለመመርመርና ለማከም ሲያስፈልግ ወደ ውስጥ ለማየት ያስችላል።
- ምርመራው ወደ ሰውነት ውስጥ አዝልቆ የማስገባት ሥራን ያካተተ በመሆኑ ሁኔታውን ዐውቆ መስማማትን በፊርማ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

# ምርመራው የሚካሄደው እንዴት ነው?





- ከምርመራው በፊት አረጋጊ አጭር ሽልብታ ፈጣሪ (አሽላቢ) ኬሚካል በመርፌ ይሰጣል።
- ምርመራው የሚካሄደው በግራ ጎን በኩል በመጋደም ነው።
- አፍን እንዲከፍት በማድረግ ጥርሶችን ለመከላከል የሚረዳ ፕላስቲክ ቁስ በጥርሶች መካከል ይደረጋል።
- ኢንዶስኮፒው በአፍ በኩል ይገባል።

המרכז הרפואי
הלל יפה
מומחים באנשים

# የጋስትሮስኮፒ ምርመራው ሂደት።




- ምርመራው የተወሰኑ ደቂቃዎችን ይወስዳል።
- በምርመራው ሂደትም የትንፋሽና የልብ ትርታ ሁኔታ ክትትል ይደረጋል።
- አንዳስፈላጊነቱ በኢንዶስኮፒው በኩል ለምርመራ ወይም ለሕክምና (ለምሳሌ ሄሊኮባክተር ፒሎሪ የተባለውን ባክቴሪያ በምመርመር ለመለየት ሲባል ቅንጣቢን ለመውሰድ) የሚሆኑ ዕቃዎች ይገባሉ።
- ከምርመራው ከተገገመ በኋላ - የውጤቶቹን ዝርዝር የያዘ መረጃ ይሰጣል።

המרכז הרפואי הלל יפה מומחים באנשים

# በኢንዶስኮፕ ሊከናወኑ የሚችሉ ሕክምናዎች



- ለምርመራ የሚሆን ቅንጣቢ (ባዮፕሲ) መውሰድ
- ፖሊፖችን መቁረጥ
- የሚደማ ቦታን መጥበስ
- ባዕድ ነገሮችን ማውጣት
- ጥበትን ማስፋት
- ደም የኀረሱ ደም ሥሮችን ማከም
- አርቲፊሻል ቱቦ ማስገባት
- መመገቢያ ቱቦ ማስገባት
- እና የመሳሰሉት

המרכז הרפואי
הלל יפה
מומחים באנשים

# ከምርመራው ጋር ግንኙነት ያላቸው እክሎች




የጋስትሮስኮፒ እክሎች ከስንት አንድ ይሁኑ እንጂ፣ ወደ ውስጥ ተዘልቆ ከሚሠሩ ሥራዎች የተነሣ ግን ሊከሰቱ ይችላሉ።

- በሚነቃነቁ ጥርሶች ላይ ዐደጋ ያስከትላል፤
- ትን መሰኘትና የምራቅ በአየር ቧምቧ መሳብ፤
- ከክንዋኔው በኋላ የጉሮሮ ህመም መሰማት፤
- መድማት እና መሸርከት የቀዶ ጥገና ጣልቃ ገብነት ይጠይቃሉ።
- ለማደንዘዣው ኬሚካል አለርጂክ መሆን፤

המרכז הרפואי
הלל יפה
מומחים באנשים

# ለምርመራው መሰናዶ የሚደረገው እንዴት ነው?




- ✓ ምግብ ሳይበላ ለ 8 ሰዓታት ያህል፣ ውሃ ሳይጠጣም ለ 3 ሰዓታት ያህል ከምርመራው በፊት መቆየት ያስፈልጋል።
- ✓ ከክፍሉ ከተለቀቅህ በኋላ አብሮህ ይሆን ዘንድ ከሰው ጋር መምጣት አለብህ።
- ✓ በማደንዘዣው ብዥታ ሳቢያ ከሕክምና በኋላ ለ 12 ሰዓታት ያህል መኪና ማሽከርከር የለም።

המרכז הרפואי הלל יפה מומחים באנשים

# ለምርመራው የሚደረግ ተጨማሪ መሰናዶ



- ✓ ከአካሚው ሐኪም ጋር የታካሚውን የቆዩ በሽታዎችና በዚህ ምረመራ ሊደረግ ያለውን የሕክምና ዐይነት ያገናዘበ ምክክር በማድረግ፣ የደም ማቅጠኛ መድኀኒቶችን፣ ምርመራው ከሚደረግበት ዕለት የተወሰኑ ቀናት በፊት ለማቆም ማሰብ ያስፈልጋል።
- ✓ የልብ ትርታ መቆጣጠሪያ መሣሪያ በውስጣቸው ላላቸው - ከጋስትሮው ክፍልና ከልብ ሐኪም ጋር አስቀድሞ በመመካከር መሰናዳት ያስፈልጋቸዋል።
- ✓ ታካሚው/ዋ ዕድሜው/ዋ ከ 18 ዓመት በታች የሆነና ዐውቆ/ቃ መስማማቱን/ቷን በፊርማው/ዋ ለማረጋገጥ የማይበቃ/ትበቃ ከሆነ/ች የወላጅ (የወኪል) ጣልቃ ገብነት ያስፈልጋል።

የጋስትሮኢንተሮሎጊያ ኮሚቴ ፍጹም ጤንነት ይመኝላችኋል፤ ይቅናችሁ።

המרכז הרפואי
הלל יפה
מומחים באנשים